ORIGINAL ARTICLE

# On the Philosophies of Zera Ya'qob and Welde Hiwot: A Comparative Analysis on Their Lessons of Social Philosophies

**Tesfu Amare (PhD)** [a]


## *Abstract*

*Philosophical thinking is one of the areas of knowledge that has existed in Ge'ez literature since ancient times. The focus of this study was to analyze lessons of social philosophies from the various concepts in the indigenous philosophical books known as Hateta Zera Ya'qob and Hateta Wolde Hiwot. According to the books, Hateta Zera Ya'qob was written by an ancient Ethiopian philosopher known in the community as Worke, also called in the Christen name Zera Ya'qob, who was born in 1592 E.C. Hateta Wolde Hiwot was also a philosophical thought which was witten by Wolde Hiwot who was a student of Zera Ya'qob. Many Europeans have written against Africans as they do not have any philosophical knowledge or ideas, and, they used this as a potent tool to make African generations lose their identities. On the contrary, this study focuses on the status of 17th century thiopian philosophy. Document review was the tool of data collection for the study, and the Ge'ez texts written by Zara Ya'qob and Wolde Hiwot have been used as sources of information. Interviews were also conducted with selected scholars to secure a better clarity. The information gathered is presented in a comprehensive analysis with qualitative approach. Accordingly, the social lessons described by Zara Ya'qob and Wolde Hiwot by were classified into their categories and presented with analysis. Finally, the study suggested the incorporation of the identified philosophical ideas in to the text books of ethical education as they contribute immensely to social building.*


**Keywords:** *Manuscript, Ge'ez, Society, Philosophy, value*


## አኅጽሮተ ጽሑፍ

የፍልስፍና አስተሳሰብ በበርካታ የግዕዝ ጽሑፎች ውስጥ የሚገኝና ከጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ጀምሮ የነበረ አንድ የዕውቀት ዘርፍ ነው። የዚህ ጥናት ትኩረት በ17ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ በፈላስፋዎቹ ዘርዐ ያዕቆብ እና ወልደ ሕይወት በተደረሱት ሀገር በቀል የፍልስፍና መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት የተለያዩ ዕሳቤዎች መካከል ማኅበረሰባዊ አስተምህሯቸውን ለይቶ በማውጣት ትንተና መስጠት ነው። ሐተታ ዘርዐ ያዕቆብ የተሰኘው ጥንታዊ መጽሐፍ እንደሚገልጸው በ1592 ዓ.ም የተወለደው በክርስትና ስሙ ዘርዐ ያዕቆብ፤ በማኅበረሰቡ ዘንድ ወርቄ በመባል ይጠራ በነበረው በጥንታዊው ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ የተጻፈ ነው። ሐተታ ወልደ ሕይወት ደግሞ የዘርዐ ያዕቆብ ተማሪ በነበረው ወልደ ሕይወት በመባል የሚታወቀው ሰው የተጻፈ የፍልስፍና ዕሳቤ ነው። ይሁን እንጂ በርካታ አውሮጳዊ ምሁራን አፍሪካውያን ምንም ዓይነት የፍልስፍና ዕውቀት ወይም ዕሳቤ የላቸውም በማለት በተደጋጋሚ ጽፈው አስነብበዋል። በዚህም ትውልዱን ማንነቱን ለማጥፋት እንደ ዋና ስልት ተጠቅመውበታል። ጥናቱ ገላጭ ንድፍን የተከተለ ሲሆን፤ ዓይነታዊ የጥናት ሥነ ዘዴን ጥቅም ላይ አውሏል። የሰነድ ፍተሻ የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ሲሆን፣ በዘርዐ ያዕቆብ እና በወልደ ሕይወት የተጻፉት የግዕዝ ጽሑፎች በመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል። የጠራ ሐሳብም ለመያዝ ከተመረጡ ምሁራን ጋር ቃለ


a. ረዳት ፡ ፕሮፌሰር (በፊሎሎጂ - የጥንታዊ ጽሑፎች ጥናት) ፤ ግእዝ ትምህርት ክፍል፤ ወሎ ዩኒቨርሲቲ

*This journal is licensed under a creative common Attribution-Noncommercial 4.0. It is accredited to the University of Gondar, College of Social Sciences and Humanities.*

**DOI:** https://dx.doi.org/10.4314/erjssh.v9i2.8

መጠይቅ ተከናውኗል። በዚህም መሠረት ጥናቱ በዘርዐ ያዕቆብ እና በወልደ ሕይወት የተገለጹትን ሐተታዎች ማኅበረሰባዊ ፋይዳዎቻቸውን በፈርጅ በፈርጃቸው በመለየት ከትንተና ጋር አቅርቧል። በመጨረሻም ጥናቱ የተለዩት የፍልስፍና ዕሳቤዎች ተወስደውና በግብረ ገብ ማስተማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተቀናጅተው ቢቀርቡ ለማኅበረሰብ ግንባታ ሊኖራቸው የሚችለውን ፋይዳ ጥቆማ ሰጥቷል።

ቁልፍ ቃላት፡- ብራና፣ ግዕዝ ፣ ማኅበረሰብ፣ ፍልስፍና ፣ ሐተታ ፣ እሴት።

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ከምትታወቅባቸው በርካታ ሀብቶች መካከል ዕድሜ ጠገብ የሆኑት በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉት ድርሳናት በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው። እ.ኤ.አ በ1997 በዩኔስኮ (UNESCO[2]) ካስመዘገበቻቸው ዐሥራ ሁለት የጽሑፍ ቅርሶች መካከል ሥምንቱ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉ ሲሆኑ፤ የጽሑፍ ቅርሶቹንም[3] ለቱሪስት መስሕብነት እየተጠቀመችባቸው፤ ምንዛሬም እያገኘችባቸው ለኢኮኖሚው ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያደረጉ መሆናቸው በግልጽ የሚታይ ሀቅ ነው። እነዚህ የጽሑፍ ሀብቶች በቁጥራቸውም በርካታ፤ በይዘታቸውም የተለያዩ በመሆናቸው፤ ለጥናት እና ምርምር የሚጋብዝ የዕውቀት ሀብት የሚታፈስባቸው ናቸው (Harden, 1926; Sergew, 1972; አምሳሉ፣ 2011)።

የጽሑፍ ሀብቶቹ ጥንታዊውን ጥበብ ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ የተለያዩ፣ የእንስሳትን ቆዳ (ብራና) ለጽሕፈት ምቹ አድርጎ የማዘጋጀት እና መልካቸው ሳይደበዝዝ እስከአሁን ቁልጭ ብለው መነበብ የሚያስችሉ የቀለም ማውጣት ችሎታ መኖሩን የሚያስረዱ ምስክሮች ናቸው (ፈቃደ ፣ 2009)። ይህም ሀገር በቀል ዕውቀት የተስፋፋ በመሆኑ በወቅቱ በርካታ የጽሑፍ ሀብቶች እንደነበሩ ያመለክታል። የጽሑፍ ሀብቶቹንም ከምንጫቸው አንጻር በሁለት መልኩ ከፍሎ መመልከት ይቻላል። የመጀመሪያዎቹ ከተለያዩ የውጭ ቋንቋዎች ማለትም ከዕብራይስጥ፣ ከግሪክ፣ ከዐረብኛ፣ ከሶርያ እና ከሮማይስጥ ወደ ግዕዝ የተተረጎሙ ሲሆኑ፤ ሁለተኛዎቹ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ጸሐፍት በወጥ ሥራነት የደረሷቸው ናቸው (Taddese, 1972; Getatchew, 2005; Harden, 1926)።

ከውጭ ቋንቋ ወደ ግዕዝ በተተረጎሙት ላይ የባለቤትነት ዕውቅና በተመለከተ ክርክር ባይኖርም፤ በኢትዮጵያውያን ጸሐፍት በወጥነት በተደረሱት ላይ ግን ውዝግብ ይነሣል። ለምሳሌ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከምትታወቅባቸው የፍልስፍና መጻሕፍት መካከል በዋናነት የሚጠቀሰውን የዘርዐ ያዕቆብን እና የወልደ ሕይወትን የፍልስፍና መጽሐፍ የባለቤትነትን ድርሻ የውጭ ሀገር ምሁራን ለአንድ አውሮጳዊ ይሰጡታል። ከእነዚህም ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ የተባለው ጣልያናዊ “የዚህ የፍልስፍና መጽሐፍ ደራሲ ጣልያናዊው ፓድሪ ጊዩስቶ ዲ ዑርቢኖ ነው” በማለት ይሞግታል። ዑርቢኖ (1847-1855) በአብዛኛው በሰሜናዊው የኢትዮጵያ ክፍል ከመኖሩም ባሻገር ግዕዝን በሚገባ መናገር፣ መጻፍ እና ማንበብ የሚችል ሰው እንደነበር ይነገራል (ብሩሕ፣ 2010)። ለዚህም ሮሲኒ እንደ ዋና ምክንያት የሚገልጸው እንደዚህ ዓይነት የፍልስፍና ዕሳቤዎችን ለማግኘት፤ በተለይም በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ባህልም ሆነ ትምህርት በዋናነት ነገረ መለኮትን ሆነ ሃይማኖትን የሚፈታተኑ ሐሳቦችን ለማፍለቅ የሚፈቅዱ አይደሉም በማለት ነበር። በተለይም በፍልስፍናው የተገለጹት ዕሳቤዎች ከኢትዮጵያ አይደለም ከአፍሪካ ምድር በዘመኑ ሊታሰቡ አይችሉም የሚል የንቀት አመለካከትም ነበረው (ጌታቸው፣ 2006፤ ዓለማየሁ፣ 1961)። ከዚህም በተጨማሪ ራሱ ፈላስፋው ዘርዐ ያዕቆብ ኢትዮጵያዊ አይደለም በማለትም ይሞግታል። እ.ኤ.አ በ1934 የተነሣው ፋገን ሚትዎች የተባለው ሰውም የፍልስፍና መጽሐፉ ደራሲ ዘርዐ ያዕቆብ አይደለም የሚለውን ሐሳብ አጠናክሮታል (Presbey & George, 2013፡10) እንደገለጹት። ከዚህም ባሻገር አስረስ (1951) የኢትዮጵያ ፊደል ከደቡብ ዐረቢያ የመጣ ነው የሚለውን ሐሳብ ያመነጨው ጣሊያናዊው ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ ነበር ይላሉ ።

ይሁን እንጂ በኋላ የተነሡ ምሁራን ለምሳሌ ዓለማየሁ (1961) እና ጌታቸው (2006) በፍልስፍና መጽሐፉ የባለቤትነት አግባብ እና በፈላስፋው ዘርዐ ያዕቆብ ፍጹም ኢትዮጵያዊነት ላይ ሐሳባቸውን ከማስረጃ ጋር በተለያዩ ጊዜያት ጽፈዋል። በተለይም በኢትዮጵያ ፍልስፍና ላይ በርካታ ሥራዎችን የሠራው ሳምነር የተባለው የፍልስፍና ምሁር ግለሰባዊ የሆነ ጥልቅ እና በሳል ዘመናዊ ፍልስፍና የተጀመረው በዘርዐ ያዕቆብ አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ሲሆን ይህም ፍልስፍናው በዘመኑ ከእንግሊዝ እና ከፈረንሳይ ፍልስፍና ጋር የተካከለ ነበር ይላል (Sumner, 1994፡227)። በተመሳሳይም (Harden, 1926:35 ) የተባለው ጸሐፊ በ17ኛው ክፍለ ዘመን አመራማሪ ይዘት ያላቸውን የዕወቀት መጻሕፍት በዘርዐ ያዕቆብ እና የእርሱ ተማሪ በነበረው በወልደ ሕይወት የተጻፉ መሆናቸውን ይጠቁማል። በማከልም ጽሑፉ ከሚሰጠው መረጃም አንጻር ከክርስቲያናዊ አስተሳሰቦች እና በተለይም በኦርቶዶክስ አማኞች ከተሠሩት ሥራዎች ወጣ ያለ መሆኑንም ይገልጻል። በተጨማሪም ሥራዎቹ ካላቸው መልእክት አንጻር ስለ ሰው ልጅ የአስተሳሰብ ታሪክ ለማጥናት አስተዋጽዖ እንዳላቸውም ይጠቁማል።

ቢሆንም የኢትዮጵያውያን የፍልስፍና የጽሑፍ ሀብቶች የሚሰጣቸው ግምት አናሳ ነው። ምክንያቱም በአጠቃላይ የአፍሪካውያን የጽሑፍ ሐሳብ

---

2 UNESCO (United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization - የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባሕል ተቋም)

3 እነዚህም ቅርሶች፡- 1. ዐራቱ ወንጌሎች (በ14ኛው መ/ክ/ዘ በግዕዝ የተጻፈ) 2. መጽሐፈ ሔኖክ (በ15ኛው መ/ክ/ዘ በግዕዝ የተጻፈ) 3. የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክቶች (በ15ኛው መ/ክ/ዘ በግዕዝ የተጻፈ) 4. ግብረ ሕማማት (በ15ኛው መ/ክ/ዘ በግዕዝ የተጻፈ) 5. ቅዳሴ (በ17ኛው መ/ክ/ዘ በግዕዝ የተጻፈ) 6. ፍትሐ ነገሥት (በ19ኛው መ/ክ/ዘ በግዕዝ የተጻፈ) 7. መዝሙረ ዳዊት (በ16ኛው መ/ክ/ዘ በግዕዝ የተጻፈ) 8. ታሪከ ነገሥት (በ20ኛው መ/ክ/ዘ በግዕዝ የተጻፈ) 9. ዐፄ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት ደብዳቤ 10. የሸዋው ንጉሥ ሣሕለ ሥላሴ ለእንግሊዝ ንግሥት የጻፉት ደብዳቤ 11. የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ታሪክ በ19ኛው መ/ክ/ዘ የተጻፈ 12. ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ለሞስኮው ንጉሥ ኒኮላስ ቄሳር 2ኛ የጻፉት ደብዳቤ (በ19ኛው መ/ክ/ዘ የተጻፈ) ናቸው።

ይዘት ከአውሮጳውያን ያነሰ ነው በማለትም ስለሚያምኑ ነው። ከዚህም ዕሳቤ በመነሣት የአውሮጳውያን የሥነ ጽሑፍ ሀብት ብቻ የበለጸገ መሆኑን ጽፈዋል (Messay, 2004) ። ከዚህም በላይ '…Africa is a land without a history of written philosophical texts, አፍሪካ የተጻፉ የፍልስፍና ጽሑፎች ታሪክ የሌላት ምድር ናት' ብለው መጻፋቸውን (Bekele and Charles, 2013) ገልጸዋል። ይህ ሁሉ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ የተሰነዘሩት ሐሳቦች የዘርዐ ያዕቆብ እና የወልደ ሕይወት የፍልስፍና ጽሑፎች የአውሮጳውያንን ሐሳብ የገዙ መሆናቸውን ልንገነዘብ እንችላለን።

የዘርዐ ያዕቆብ እና የወልደ ሕይወት ፍልስፍና ዕሳቤዎች ከተለያዩ የፍልስፍና ዐውዶች አንጻር ሊመነዘሩ የሚችሉ ሐሳቦችን ያዘሉ ቢሆንም በዚህ ጥናት ግን በማኅበረሰባዊ ፍልስፍና ዙሪያ በሚያጠነጥኑት ሐሳቦች ላይ ተተኩሯል። የፍልስፍና አጥኝዎች ማኅበረሰባዊ ፍልስፍናን በተለያዩ ሁኔታዎች ተርጉመውታል (Pedersen, 2012; Saar, 2018)። እንደ ሜሪያም -ዌብስተር መዝገበ ቃላት[4] ብያኔ ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና ማኅበረሰብን እና ማኅበረሰባዊ ተቋማትን ከሚታየው ግንኙቶቻቸው ይልቅ ከሥነ ምግባራዊ ዕሴቶቻቸው አንጻር የሚያጠና እና የሚተረጉም ዘርፍ ነው። ከዚህ ብያኔ አንጻር ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና የሰው ልጅ ስላለው ሥነ ምግባራዊ ዕሴት ማለትም ለማኅበረሰብ ደግ ወይም ክፉ ነገር ምንድን ነው ብሎ የሚመረመር የፍልስፍና ዘርፍ መሆኑ ላይ ያተኩራል። በተመሳሳይ ሐሳብ (Audi, 2005) ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና በማኅበረሰብ ውስጥ ለሰው ልጅ ደግ ስለሚሆንለት ነገር በትኩረት እንደሚያጠና ይገልጻል። የሰው ልጅ ማኅበራዊ እንስሳ ሲሆን ማኅበረሰባዊ የሚባለውም ለመኖር፣ ለመባዛት፣ ለማደግ፣ ወዘተ. ከሌላው አካል ጋር የግድ መገናኘት ስለሚኖርበት ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው ብቻውን ሙሉ ሊሆን ስለማይችል ነው። ስለዚህም ፈላስፋው ዘርዐ ያዕቆብ (በክፍል 8) ላይ "እግዚአብሔር አስተዋዮችና የተሟላን ሆነን ፈጣሪያችን በጥበቡ ላዘጋጀልን ዋጋ የተገባን እንድንሆን በዚህ ዓለም ባለንበት ጊዜ ለማሟላት አስተዋዮችና ዝግጁዎች አድርጎ እንድንሟላ ፈጠረን እንጂ የተሟላን አድርጎ እንዳልፈጠረን ልናውቀው ይገባናል" ይላል። ከዚህ አንጻር ማኅበረሰባዊነት ለመሟላት የግድ የሚያስፈልግ መስተጋብር መሆኑን እንረዳለን። በአጠቃላይ ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና በማኅበረሰቡ ውስጥ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሔ ለማመላከት ሰዎች በሚያደርጓቸው ሰብአዊ ግንኙነቶች እንዴት መሆን እንዳለበት ጠቋሚ ሐሳብ የሚያመላክት የፍልስፍና ዓይነት ነው ማለት ይችላል።

የዘርዐ ያዕቆብ እና የወልደ ሕይወት ፍልስፍና መጽሐፎች በተለይም በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያን ማኅበረሰብ ዘንድ ጎድለው የሚታዩ መስተጋብሮች እንዴት መሟላት እንደሚችሉ እና እንደሚገባቸው የሚረዱ ሐሳቦች እና በበርካታ ዐውድ ተመንዝረው መታየት የሚችሉ ዕምቅ ዕውቀትን ያዘሉ ናቸው። በእነዚህ መጽሐፎች ላይ በርካታ አጥኚዎች ትኩረታቸውን ያደረጉት የፍልስፍና መጽሐፎቹ በዓለማችን ላይ ከሚታወቁት የፈላስፋዎች አስተሳሰብ ጋር የሚተካከል ሐሳብ የያዘ መሆኑ ላይ ያተኩራል (ብሩሕ፣ 2010)። ነገር ግን የዘርዐ ያዕቆብ እና የተማሪው ወልደ ሕይወት የፍልስፍና መጻሕፍት ኢትዮጵያዊ ከመሆናቸው ባሻገር ያዘሉት ሐሳብ ለማኅበረሰቡ ሊያበረክተው ከሚችለው ቁም ነገር አንጻር ግን በፈርጁ በፈርጁ ተለይቶ ራሱን ችሎ ሲቀርብ አይስተዋልም። ከዚህ አንጻር የዘርዐ ያዕቆብ እና የወልደ ሕይወት የፍልስፍና መጽሐፎች የያዙትን ለማኅበረሰብ ሊያስተምሩ እና ሊበጁ የሚችሉ የፍልስፍና ዕሳቤዎችን ለይቶ በማውጣት ከትንተና ጋር ለማቅረብ ጥናቱ አስፈላጊ ሆኖ ተከናውኗል።

## የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የዘርዐ ያዕቆብ እና የወልደ ሕይወት የፍልስፍና መጻሕፍት ከያዟቸው የፍልስፍና ዕሳቤዎች ውስጥ ማኅበረሰባዊ አስተምህሮዎቻቸውን ለይቶ በማውጣት ተንትኖ ማቅረብ ነው።

## የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በዋናነት ሁለት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል። የመጀመሪያው በ17ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ኢትዮጵያውያን ፈላስፎች ዘርዐ ያዕቆብ እና ወልደ ሕይወት በጻፏቸው ሁለት የፍልስፍና መጽሐፎች ውስጥ ለማኅበረሰቡ ሊያበረክቷቸው የሚችሉ አስተምህሮዎች ተለይተው ስለቀረቡ መልካም ማኅበረሰብን ለመፍጠር ጠቀሜታ ይኖረዋል። በሁለተኛው በጥንታዊው ዘመን የኢትዮጵያውያን የፍልስፍና እና የሥነ ጽሑፍ ዕድገት ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር አንባቢዎች እንዲረዱ ሊያግዝ ይችላል።

## ክለሳ ድርሳን - ፍልስፍና እና ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና ንድፈ ሐሳባዊ ገለጻ

የዚህ ጥናት ማጠንጠኛ ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና ነው። በዚህ ክፍል ስለፍልስፍና እና ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና ንድፈ ሐሳባዊ ምንነት የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ተደርጓል።

4 Social Philosophy: the study and interpretation of society and social institutions in terms of ethical values rather than empirical relations. "Social philosophy." Merriam-Webster.com Dictionary, Merriam-Webster, https://www.merriam webster.com/dictionary/social%20philosophy. Accessed on 24 Sep. 2021.

## ፍልስፍና (Philosophy) ምንድን ነው?

ፍልስፍና (Philosophy) የሚለው ቃል ከግሪክ የተወሰደ ቃል ሲሆን ይህም 'የጥበብ ፍቅር' ወይም 'ጥበብን መውደድ' ተብሎ ቃል በቃል ሊተረጎም ይችላል። ፍልስፍና የሰው ልጅ የአስተሳሰብ ልሕቀት መገለጫ ሲሆን ለዚህም ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ ብስለት እና የመመርመር ክህሎትን የሚጠይቅ የማሰብ ሥራ ነው። መሳይ "ፍልስፍና ግላዊ፣ በሳል እና ሒደታዊ ጽብረቃ" (Philosophy is an individual, critical, and systematic reflection) መሆኑን ሲጠቁም (Messay, 2004፡ 99)፤ ኢያሱ (2009) ፍልስፍና ማለት በሥነ አመክንዮ መነጽር እና ጥልቅ በሆነ ሐተታ፣ በተጠየቃዊ ዘይቤ የሕይወትን ትርጉም የተፈጥሮን ምሥጢር ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ ችግሮች ወዘተ. የተመለከቱ ጉዳዮችን እያነሡ መወያየት፣ መመርመር፣ መጠየቅ፣ መሞገት፣ መተቸት ነው ይላል። በተመሳሳይም ብሩሕ (2010) ፍልስፍና ጥልቅ ሐሳብ የያዙ የፍልስፍና ጥያቄዎችን እያነሣ መልስ የሚሰጥ ሐሳብ ነው ይላል። ከዚህ አንጻር ፍልስፍና ዓላማው ለማወቅ የሚደረግ ፍላጎት እና ተግባራዊ ጥረት በመሆኑ የሚዳሰሰው ርእሰ ጉዳይ የተገደበ አይደለም። ስለዚህም (Audi, 2005) እንዲህ ይላል፡-

> Philosophy … is the critical, normally systematic study of an unlimited range of ideas and issues… Philosophy pursues questions in every dimensions of human life, and its techniques apply to problems in any field of study or endeavors. It may be described in many ways. It is a reasoned pursuit of fundamental truths, a quest for understanding, and a study of principles of conduct. It seeks to establish standards of evidence, to provide rational methods of resolving conflicts, and to create techniques for evaluating ideas and arguments. Philosophy may examine concepts and views drawn from science, art, religion, politics, or any other realm.

ፍልስፍና ነገሮችን በጥልቀት ለማወቅ የሚረዳ ከፈጣሪ ለሰዎች የተሰጠ ጸጋ ስለመሆኑም ዘርዐ ያዕቆብ "አስተዋዮች አድርጎ የፈጠረን ከአስተዋይነቱ በተትረፈረፈው (አስተዋይነቱ) ነው።" ይላል (ክፍል3) ላይ። ከዚህም ባሻገር ሰዎች ነገሮችን ከመረመሩ በኋላ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ የሚጋብዝ የዕውቀት ዘርፍ ስለመሆኑም "ለተመራማሪ ግን እውነት ፈጥና ትገለጣለች።" ይላል (ክፍል 5)። እንደ ዘርዐ ያዕቆብ 'እውነት' የሚለው አንድ ሰው ከመረመረ በኋላ በመጨረሻ የሚደርስበትን ድምዳሜ ነው። ይህ ጥልቅ በሆነ ስሜት ከአንድ ግለሰብ የመነጨ አስታሰብ እያደገ በማኅበረሰቡ ውስጥ ቅቡል እየሆነ ሲመጣ የጋራ ሐሳብ እየሆነ ይመጣል። በአጠቃላይ ፍልስፍና ማለት የሰው ልጅ ባልተገደበ ሐሳብ ወይም ጉዳይ ላይ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ በመጠየቅ፣ በመከራከር፣ በመወያየት፣ በመመርመር፣ ወዘተ. ወደ ድምዳሜ በመድረስ ዕውቀት የሚገኝበት ዘርፍ ነው።

## ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና

የሰው ልጅ ለመኖር በማኅበረሰቡ ውስጥ መስተጋብር (ግንኙነት) መፍጠር ግድ የሚለው ፍጡር ነው። ማኅበረሰቡም እሱን እየቀረጸ ራሱን የቻለ ሰው እንዲሆን ያደርገዋል (Verharen, 1996)። ይህ ሰብኣዊ ግንኙነት በፍልስፍና ዐውድ የሚጠና ሲሆን፤ ይህም ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና ይባላል። ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና ማለት በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለ የሰዋዊ ግንኙነቶች ፍልስፍና ነው (Saar, 2018)። እያንዳንዱ ማኅበረሰብ በአስተሳሰብ የበለጸጉ ጠቢባን ወይም ፈላስፋዎች አሉት። ከእነዚህ ፈላስፋዎች የሚመነጨው አስተሳሰብ በማኅበረሰቡ ዘንድ ቅቡልነት ሲያገኝ በማኅበረሰቡ ሕይወት ውስጥ የራሱ የሆነ ሚና ይጫወታል። ይህ የግለሰብ አስተሳሰብ (ፍልስፍና) እየተዋወቀ እና እያደገ ሲመጣ የጋራ ዕወቀት እየሆነ፤ ማኅበረሰብንም እርስ በእርስ ለማስተሳሰር አስተዋፅዖው የጎላ እየሆነ ይመጣል (ኢያሱ፣ 2009)። በጊዜ ሒደትም የጋራ ሀብት ከመሆን ባሻገር የሀገር መታወቂያም ከመሆን ይደርሳል። በዚህም ለምሳሌ ያህል የግሪክ ፍልስፍና፣ የአውሮጳ ፍልስፍና፣ የቻይና ፍልስፍና፣ የኢትዮጵያ ፍልስፍና ወዘተ. እየተባለ የሚጠራው ፍልስፍና ከግለሰብ አልፎ ሀገርን የገዛ ሐሳብ በመሆኑ ነው።

ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና የአንድ ሀገርን ሕዝብ ምን ያህል እንደሚያስተሳስር ሀገራችንን ኢትዮጵያን ወስደን እንመልከት። ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ ባለቤት እንዲሁም የተለያየ መልክአ ምድር እና በልዩ ልዩ እሴቶች የሚገለጡ የተለያዩ ባህሎች ያላቸው ማኅበረሰቦች ሀገር ናት። ሌቪን የተባለው አጥኚ በተመሳሳይ ስለኢትዮጵያ በጻፈው እንዲህ ይላል፡ "… to see Ethiopia as a mosaic of distinct peoples is to overlook the many features they have in common and the existence of discernable culture, and to ignore the numerous reationships these groups have had with one onother" (Levin, 1974፡21)። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች የየራሳቸው የሆነ የማንነት መገለጫ አላቸው። ቢሆንም ይህ መገለጫ በተለያዩ ክስተቶች ለምሳሌ በንግድ እና ከቦታ ወደ ቦታ በሚደረግ እንቅስቃሴ ያላቸውን ባህል እና እሴት ከሌላው ጋር በማጋባት የሚኖሩ በመሆናቸው በመካከላቸው የባህል ልዩነቱ የጎላ አይደለም ብለው በአጽንዖት የሚናገሩ አሉ (ተክለ ጻድቅ፣ 1951፡14; Sumner,1985:2)። ይህንንም ዕይታ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በተለያዩ መስተጋብሮች የተዋሐዱ፤ በልዩነት ውስጥ አንድነት ያላቸው ሕዝቦች መሆናቸውን ልንረዳበት እንችላለን።

ከዚህም ሁኔታ በመነሣት የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚታወቁበት ራሱን የቻለ ከፍ ያለ ማኅበራዊ መስተጋብርን የፈጠረ አስተሳሰብ አላቸው። ይህ ከፍ ያለ አስተሳሰብ የኢትዮጵያ ፍልስፍና ይባላል (ኢያሱ፣ 2009)። ፍልስፍናውም ለምሳሌ ስለተፈጥሮ በሚደረገው ምርምር (ሐተታ ተፈጥሮ) ማኅበራዊ መስተጋብርን ለመበየን፣ ሕይወትን ለመተርጎም፣ ደስታ ሐዘንን ለመግለጽ፣ ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ ችግሮችን ለመፍታት ሰዎች ከሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት እና የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር በሚያደርገው ቁርኝት በዘመን ሒደት ውስጥ በሚኀለብቱ ሀገር በቀል ዕወቀቶች ውስጥ ፍልስፍናን ማግኘት እንችላለን (ዝኒ ከማሁ)። ከዚህም ባሻገር ዘመን ተሻጋሪ በሆኑ ተረቶች፣ እንቆቅልሾች፣ የሙግት ደንቦች፣ የዕርቅ እና ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓቶች፣ ሥነ ቃሎች፣ ቅኔዎች ውሰጥ የሚገኙ የላቁ አስተሳሰቦች ፍልስፍና ናቸው። እነዚህ ሁሉ ማህበረሰብን የሚገነቡ እና የሚያስተሳስሩ ሀገር በቀል አስተሳሰቦች ማኅበራዊ ፍልስፍና ይባላሉ።

## በዘርዐ ያዕቆብ ፍልስፍና ላይ የተነሡ ውዝግቦች

ዘርዐ ያዕቆብ በጻፈው የፍልስፍና መጽሐፍ ላይ በርካታ ውዝግቦች መነሣታቸው ይታወቃል። የዚህ ውዝግብ ዋና መነሻ አውሮጳውያኑ ለአፍሪካዊ አስተሳሰብ የሚሰጡት ግምት አናሳ መሆኑ ነው። አውሮጳውያን አፍሪካን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ከገቡ ጀምሮ በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ የተመለከቷቸው የብራና መጻሕፍት ቀልባቸውን ከሳቧቸው ውስጥ ዋነኞቹ ነበሩ። ከእነዚህም አባዲ[5] እና ዑርቢኖ[6] የተባሉት የብራና መጻሕፍትን ሰብስቦ ወደ ሀገራቸው በማጋዝ የተጠመዱ ነበሩ። አባዲ በ1849 በርካታ የብራና መጻሕፍትን ይዞ ወደ ሀገሩ ፓሪስ ሲመለስ፤ ዑርቢኖ ደግሞ በጎንደር አካባቢ ነበር። ዑርቢኖ ከአንድ ታጣቂ አንድ የግዕዝ ብራና መጽሐፍ ሁለት ቅጅዎችን ገዝቶ ለጓደኛው አባዲ በየካቲት ወር 1853 እ.ኤ.አ. ወደ ፓሪስ ይልክለታል (ጌታቸው 2006፡55)። አባዲ ለብዙ ጊዜያት ሁለቱን የብራና መጻሕፍቶች የግሉ ንብረቶች አድርጎ አስቀምጧቸውም ነበር። አባዲም ከሞተ በኋላ ‘D’Abbadie’ 215 እና ‘D’Abbadie’ 234[7] የሚል መለያ ተሠጥቷቸው በፓሪስ ብሔራዊ ቤተመጻሕፍት ውስጥ ተቀመጡ።

ዑርቢኖ እነዚህን ሁለት ቅጅዎች ለአባዲ ሲልክለት በየጥራዞቻቸው ላይ ማስታወሻ ጽፎባቸው ነበር። ይህም ‘D’Abbadie’ 215 “በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ ግለ ታሪክን መጻፍ የተለመደ አይደለም” ሲል ‘D’Abbadie’ 234 ደግሞ “ይህን መጽሐፍ የኢአማኒነት አስተሳሰብ ማካተቱ ያልተለመደ ያደርገዋል” የሚል ነበር (ዝኒ ከማሁ)። ይህ ከሆነ በኋላ ኮንቲ ሮሲን በ1916 ዘርዐ ያዕቆብ ኢትዮጵያዊ አይደለም የሚል ጭብጥ የያዘ መጽሐፍ ጻፈ። ለዚህም ማስረጃ ያደረገው በዘመኑ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት የተቀላቀሉትን የአባ ተክለ ሃይማኖትን ምስክርነት ነበር። የአባ ተክለ ሃይማኖት ምስክርነትም፡- ዑርቢኖ ከቅኔ ጀምሮ እስከ መጻሕፍት ትርጓሜ ድረስ የተማረ ሲሆን፤ ይህን የፍልስፍና መጽሐፍ ከአንድ ወታደር ገዛሁት ይበል እንጂ መጽሐፉን በወርቄ ስም የደረሰው ራሱ ዑርቢኖ ነው የሚል ነበር (ሰምነር 1976፡ 65)። በተለይም ሮሲኒ ድርሰቱ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ላይ ከሚያደርገው ያልተለመደ ክርክር በመነሣት ይህ አስተሳሰብ ከኢትዮጵያውያን ባህል እና ሃይማኖት ሊመነጭ አይችልም የሚል ነበር።

ይህንንም የባለቤትነት ሽሚያ ሮሲኒ ከኢትዮጵያ አውጥቶ ለአውሮጳዊ ለመስጠት አስረጅ አድርጎ ቢጠቀምበትም ከላይ እንደተመለከትነው አባዲ በየጥራዞቹ ላይ ሐሳቡን ሲያስቀምጥ የራሱ ሥራዎች መሆናቸውን ግን አልጠቀሰም። አባ ተክለ ሃይማኖትም ቢሆኑ በሰጡት “ምስክርነት” እንዲሁ ዑርቢኖ ነው ይበሉ እንጂ ዑርቢኖ ሲጽፍ አይቻለሁ፤ ወይም የተመለከተ ነግሮኛል አላለም (ዝኒ ከማሁ)።

በአንጻሩ ደግሞ ዘርዐ ያዕቆብ ፍጹም ኢትዮጵያዊ ስለመሆኑ ዓለማየሁ (1961) እና ጌታቸው (2006) የየራሳቸውን አመክኔያዊ መከራከሪያ ሐሳቦቻቸውን ሰጥተዋል። ሁለቱም ምሁራን በዋናነት የሚጋሩት ዘርዐ ያዕቆብም እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለመዝሙረ ዳዊት የሚሰጠው ቦታ ትልቅ በመሆኑ በፍልስፍናው ውስጥ ቃል በቃል በመጥቀስ እና ሲሰደድም እንደ መጽሐፍ መምህርነቱ በርካታ መጽሐፍ እንደሚኖሩት ቢጠበቅም ይዞ የተሰደደው ግን መዝሙረ ዳዊትን ብቻ ነበር። በተቃራኒው ደግሞ በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ዳዊትን ለጸሎት መጠቀም የተለመደ አይደለም። ስለዚህ ዘርዐ ያዕቆብ ኢትዮጵዊ በመሆኑ ለመዝሙረ ደዊት የሰጠው ድርሻ የጎላ ሆኗል። በተጨማሪም ዓለማየሁ (1961) ዑርቢኖ ኢትዮጵያ ውስጥ የኖረው ለስምንት ዓመታት ብቻ ሲሆን ወደ ግእዝ ትምህርት ያቀናው በመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመታት ብቻ በመሆኑ እነዚህ ዓመታት ቅኔን ለመማር እና ሐተታውን ለመጻፍ በቂ አይደሉም በማለት ይሞግታል። ሦስተኛም በሐተታው ውስጥ የሚገኘው የቋንቋ መዋቅር ሲሆን በዚህም ጸሐፊው የግዕዝ ቅኔን በከፍተኛ ሁኔታ የተማረ መሆኑን መረዳት ይቻላል። በመሆኑም ዘርዐ ያዕቆብ በሐተታው ውስጥ የጻፋቸው ዓረፍተ ነገሮች የባለቤት፣ ግሥ እና ተሳቢ አወቃቀር የራሱ እንጂ የሌላ (የውጪ ዜጋ) መሆናቸውን አያሳዩም (ዝኒ ከማሁ)።

ከዚህም ባሻገር ጌታቸው (2006፡10) እንዲህ ይላሉ፡ “በሚታመን ማሰረጃ የሚከራከርለት አጥቶ ነው እንጂ ወርቄስ (ዘርዐ ያዕቆብስ) ኢትዮጵያዊ መሆኑስ አያጠራጥርም”። ለዚህም በመጀመሪያ የሰጡት ማስረጃ በሀገራችን ልማድ አንድ ክርስቲያን በዓለም የሚጠራበት ስምና የክርስትና ስም ቢኖሩትም በዘወትር የሚጠራው ግን በዓለማዊ ስሙ ነው። በዚህም ልማድ ዘርዐ ያዕቆብ ሐተታውን ሲጽፍ “… ወበጥምቀተ ክርስትና ተሰመይኩ ዘርዐ ያዕቆብ ወሰብእሰ ይቤሉኒ ወርቄ።” ትርጉም፡ “በክርስትና ጥምቀት ዘርዐ ያዕቆብ ተባልኩ፤ ሰዎች ግን ወርቄ ይሉኛል።” ከዚህ

---

5 አባዲ (Antoine d’Abbadie) ከ1837-1849 በሰሜናዊው የኢትዮጵያ ክፍል በተለይ በጎንደር አካባቢ በአሳሽት የሠራ ነበር።

6 ዑርቢኖ (Padre Giusto d’Urbino) ደግሞ ጣሊያናዊ መነኩሴ ሲሆን ከ1847-1855 ከአባዲ ቀጥሎ በሰሜን ኢትዮጵያ የኖረ ፈረንሳዊ ነበር። (Claude Sumner, 1976: P.65 and ጌታቸው ኀይሌ: 2006 )

7 ‘D’Abbadie’ 215 ሁለቱንም የዘርዐ ያዕቆብን እና የወልደ ሕይወትን ፍልስፍናዎች የያዘ ሲሆን፤ ‘D’Abbadie’ 234 ደግሞ የዘርዐ ያዕቆብን ብቻ ያዘ ነበር።

አንጻር ወርቄነቱን ትቶ በዘርዐ ያዕቆብ እንዲታወቅ ያደረገው ዑርቢኖ ነው። ስለዚህ ዘርዐ ያዕቆብ (ወርቄ) ኢትዮጵዊ ነው ይላሉ። በማከልም በሁለቱ ቅጅዎች ማለትም በ'D'Abbadie 215' እና በ'D'Abbadie 234' ውስጥ ዘርዐ ያዕቆብ የልጅ ልጅ ያየበትን የተለያየ ቀን መጠቀሱን ነው። ይህም በD'Abbadie' 215 ላይ ሰኞ ጥቅምት 11፣ 1631 ሲል በ'D'Abbadie 234' ደግሞ ሰኞ ጥቅምት 10፣ 1631 ይላል። በዚህም 234ቱን ራሱ ዑርቢኖ የገለበጠው ነው። ዑርቢኖ የቀኑን ቁጥር ሲቀይር ያረጋገጠው ሰኞ እና ጥቅምት 10 መገጣጠሙን ብቻ እንጂ ዓመተ ምሕረቱን አላስተዋለም። ሆኖም ግን ጥቅምት 10 ሠኞ ላይ የሚውለው በ1844 ዓ.ም ብቻ ነው። የ215ቱ ቅጅ ዋናው መጽሐፍ ላይ ያለውን ትክክለኛ ቀን የሚያሳይ ሲሆን፤ የ234ቱ ቅጂ ደግሞ የተቀዳበትን ትክክለኛ ቀን ያሳያል። ይህም ቀን ሠኞ ጥቅምት 10፣1844 ዓ.ም ነው። ከዚህ አንጻር ሐተታ ዘር ያዕቆብ የ19ኛው መ/ክ/ዘመን መጽሐፍ ሳይሆን የ17ኛው መ/ክ/ዘ መጽሐፍ መሆኑን ያሳያል። በመሆኑም ኮንቲ ሮሲኒ ሐተታ ዘርዐ ያዕቆብ የ19ኛው ክ/ዘመን መጽሐፍ ነው ብሎ ያቀረበው ነገር ተቀባይነት የለውም። የ19ኛው መ/ክ/ዘመን መጽሐፍ ካልሆነ ደግሞ ጸሐፊው ዑርቢኖ አይደለም ማለት ነው። ምክንያቱም ዑርቢኖ የኖረው በ19ኛው መ/ክ/ዘመን ስለሆነ።

ከዚህም ጋር ስለ ዘርዐ ያዕቆብ ኢትዮጵያዊነት የራሴንም እይታ እሰጣለሁ። የመጀመሪያው ዘርዐ ያዕቆብ የሚለውን ጥምር ቃል (ዘርፍ እና ባለቤት) አድርጎ መጥራት በአውሮጳውያን ስም ዘንድ የተለመደ አይደልም። ስለዚህ ይህ አይነት ስም አጠራር ፍጹም ኢትዮጵያዊ መሆኑን ስለሚያሳይ ዘርዐ ያዕቆብ ፍጹም ኢትዮጵያዊ ነው የሚል ሐሳብ መያዝ ይቻላል። ሁለተኛው ደግሞ ከላይ እንደተመለከትነው ዓለማየሁ ሞገስና ጌታቸው ኀይሌ ዘርዐ ዕቆብ ለመዝሙረ ዳዊት ያለው አክብሮት እና ለጸሎትም ሆነ ለሐተታው ማጣቀሻነት እንዳለ መጠቀሙ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ያሳያል ካሉት ጋር በማስማማት፤ ዘርዐ ያዕቆብ መዝሙረ ዳዊትን እያጻፈ ጥቅም ማገኘቱን ይገልጻል፤ በተደጋጋሚ የጻፈው መዝሙረ ዳዊትን መሆኑንም እንረዳለን። እስከ አሁንም ድረስ አንድ የብራና ጸሐፊ ከጻፋቸው ብራናዎች ከፍተኛ ቁጥሩን የሚይዘው መዝሙረ ዳዊት መሆኑ ግልጽ ነው። ምክንያቱም ከሌሎቹ መጻሕፍት በላይ ጥቅም ላይ የሚውለው መዝሙረ ዳዊት ስለሆነ ነው። ስለሆነ ዘርዐ ያዕቆብም ወደዚህ ሥራ ማተኮሩ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ነው ማለት ይቻላል።

## የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ በጽሑፍ ሥራ ላይ ስለሚያተኩር ዓይነታዊ የጥናት ሥነ ዘዴን ተጠቅሟል፤ ገላጭ ንድፍንም ተከትሏል። ለጥናቱም የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮች በዘርዐ ያዕቆብ እና በወልደ ሕይወት በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍት ናቸው። የሁለተኛ ደረጃ ምንጮች መጻሕፍት፣ የታተሙ እና ያልታተሙ የምርምር ጽሑፎች ናቸው። በተጨማሪም ሐሳብን ለማጠናከሪያነት እና የጠራ ሐሳብ ለመያዝ ከተመረጡ የቤተክህነት እና የዘርፉ (የፍልስፍና) ምሁራን ጋር ቃለ መጠይቅ ተከናወኗል። በመሆኑም የተሰበሰቡት መረጃዎች በየጭብጣቸው እየተደራጁ የቀረቡ ሲሆን ለየት ያሉ ሐሳቦች ራሳቸውን ችለው እንዳለ ተቀምጠዋል። እንደ አጠቃላይም ጥናቱ የተመሠረተው በሐሳብ ትንተና ላይ በመሆኑ ሐተታዊ በሆነ መንገድ በገለጻ የትንተና ዘዴ ተትንትኖ ቀርቧል።

## ትንተና በማኅበረሰባዊ ፍልስፍና አስተምህሮዎች ላይ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በዘርዐ ያዕቆብ እና በወልደ ሕይወት የፍልስፍና መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና አስተምህሮዎችን በመለየት ትንተና መስጠት ነው። ነገር ግን ድርሰቶቹ በተለያዩ የሞያ ዐውዶች ሊመነዘሩ የሚችሉ የፍልስፍና አስተሳሰቦችን የያዙ መሆናቸውን ልብ ይሏል። በአጠቃላይ ከይዘታቸው አንጻር ሲታዩ የወልደ ሕይወት ሐተታ የዘርዐ ያዕቆብን ሐሳብ መሠረት ያደረገበት (ተመሳሳይነት)፣ ሐሳቡን አሻሽሎ ያቀረበበት እና በአንዳንዶችም ላይ የተለያዩበት ዕሳቤ እንዳለ ማስተዋል ይቻላል። ለምሳሌ፡-

**ተመሳሳይነት፡-** ዘርዐ ያዕቆብ (በክፍል 5) ላይ "ለተመራማሪ እውነት (ዕውቀት) ፈጥና ትገለጻለች" ሲል ወልደ ሕይወት ደግሞ (በክፍል 2 ላይ) "ሳትመረምር ልታውቅ አይቻልህም ይላል" ከዚህ አንጻር እውነት (ዕውቀት) የምርምር ውጤት ስለመሆናቸው ሁለቱም ይስማማሉ።

**የሐሳብ መሻሻል፡-** "ፈጣሪ አለን?" በማለት ለሚያነሣው የፍልስፍና ጥያቄ ዘርዐ ያዕቆብ ሲመልስ " ፈጣሪስ አለ ፈጣሪ ከሌለ ፍጥረት ባለተገኘ ነበር …" (በምዕራፍ 3) ሲል ለዚሁ ተመሳሳይ ጥያቄ ወልደ ሕይወት ደግሞ "ያለ ፈጣሪ ፍጡር መሆን እንዴት ይቻላል"። (በክፍል 3) በማለት ወልደ ሕይወት ሐሳቡን ከፍ እንዳደረገው ልብ ይሏል።

**የሚለያዩበት፡-** ዘርዐ ያዕቆብ የሀብቱ አገልጋይ የነበረችውን ለሚስትነት ሲጠይቀው ሀብቱም "እሺ አገልጋይህ ትሁንህ ሲለው" ዘርዐ ያዕቆብ ግን "ሚስቴ ትሆናለች እንጂ አገልጋዬስ አትሆንም። ምክንያቱም ወንድ እና ሴት በጋብቻ እኩል ናቸው። አንድ አካል አንድ ኅብረት ናቸውና ጌታና አገልጋይ ልንላቸው አይገባም" (በክፍል 12) ሲል ወልደ ሕይወት ደግሞ (በክፍል 26) ላይ "ሴቶች በተፈጥሮ ከወንዶች ደካማ እንደሆነች አስብ" ይላል። በዚህም የዘርዐ ያዕቆብ እሳቤ የወንድ እና የሴት እኩልነት የተንጸባረቀበት ሲሆን፤ በወልደ ሕይወት እሳቤ ግን ወንድ እና ሴት በአፈጣጠራቸው ፍጹም የተለያዩ መሆናቸውን፤ ሴቶች ከወንዶች የሚያንሱ መሆናቸውን ስለሚገልጽ የሐሳብ ልዩነታቸው ጎልቶ ይታያል።

ከዚህ ቀጥሎ በተለያዩ ማኅበረሰብን ሊያንጹ፤ ሊያስተምሩ እና ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል ሊጋራባቸው የሚችሉት ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## ስለሃይማኖት መከባበር

ዘርዐ ያዕቆብ በትምህርት ዘመኑ የካቶሊክን እና የኦርቶዶክስን ትርጓሜ የተማረ ሲሆን፤ ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው ትምህርት የየራሳቸው ብቻ ትክክል እንደሆነ ይነግሩት ነበር። ነገር ግን ይህ እንዳልተስማማው ይገልጻል። በተለይ አንዱ ሌላውን ሲከስስ እና ሲያሳድድ ሲመለከት ሁኔታው ይበልጥ ያሳዝነው ነበር። በኋላም የትኛዋ ሃይማኖት ትክክል እንደሆነች ይመረምር፤ይጠይቅም ነበር። ስለዚህም ዘርዐ ያዕቆብ እንዲህ ይላል፡-

> እኔም መጀመሪያ ስለ ብዙ የሃይማኖታችን ነገር አንዱን የፈረንጅ መምህር ጠየቅሁት። እሱም ሁሉንም ነገር ከራሱ ሃይማኖት አንጻር ተረጐመው። ቀጥዬ ደግሞ አንዱን ትልቅ ኢትዮጵያዊ መምህር ጠየቅሁት። እሱም ሁሉንም ነገር ከራሱ ሃይማኖት አንጻር ተረጐመው። እስላሞቹንና አይሁዶችንም ብንጠይቅ እነሱም እንደዚሁ ከሃይማኖታቸው አንጻር ነው የሚረዱት። እንደዚህ ከሆነ ታዲያ እውነትን የሚፈርድ ከየት አገኛለሁ? ምክንያቱም ሃይማኖቴ ለእኔ እውነት እንደሚመስለኝ ሁሉ ለሌላውም እንዲሁ የራሱ ሃይማኖት ብቻ እውነት ይመስለዋል። እውነት ግን አንድ ናት። ... (ክፍል 4)

የእሱም ተማሪ የሆነው ወልደ ሕይወት ደግሞ (ክፍል 6) ላይ እንዲህ ይላል፡-

> አንዱ በእስክንድርያ ሃይማኖት እመኑ ይለናል። ሁለተኛው በሮም ሃይማኖት እመኑ ይሉናል። ሦስተኛው በእስልምና በመሐመድ ሃይማኖት እመኑ ይለናል። ዐራተኛው በሙሴ ሃይማኖት እመኑ ይለናል። የሕንድ ሰዎችም እንዲሁ ልዩ ሃይማኖት አላቸው። የሕምያር ሰዎችና የሳባ ሰዎች ሌሎችም እንዲሁ ሁላቸው ሃይማኖታችን ከእግዚአብሔር ነው ይላሉ። ...

ከዚህ አንጻር የዘርዐ ያዕቆብ እና የወልደ ሕይወት ዕሳቤ ሁሉም ሃይማኖት በተከታዩ ዘንድ ለራሱ (ለአማኙ) ብቻ ትክክል መሆኑን እንጂ በሌላው ዘንድ አለመሆኑን በመረዳት አንዱ የሌላውን ሃይማኖት ማክበር እንዳለበት ያስረዱናል። በተመሳሳይም ሁለቱም ፈላስፎች ሃይማኖት የሰው ልጅ በተሰጠው አዕምሮ መርምሮ እውነቱን በዕውቀት ተመሥርቶ ሲያገኝ እና ከተፈጥሮ ባሕርዩ ጋር ሲስማማ የሚያምንበት መሆን እንዳለበት ይጠቁማሉ (ዘርዐ ያዕቆብ ክፍል 4 እና የወልደ ሕይወት ክፍል 6)። በተለይም ዘርዐ ያዕቆብ ማዕከላዊ በሆነ አስተሳሰብ ሁሉም ሰዎች በሚከተሉት ሃይማኖት የፈጣሪ መኖርን ስለሚቀበሉ በዚህ አስተሳሰብ አንድ ሊሆኑ እና ከመከባበር አልፎ ሊያፋቅራቸው እንደሚችል ያስረዳል። ስለዚህም (ክፍል 6) ላይ እንዲህ ይላል፡-

> .... ምንም እንኳን ሰዎች በሃይማኖት ባይስማሙም በአንድ ነገር ግን ይስማማሉ። በፈጣሪ መኖር። እስኪ እናስብ ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር አለ በሚለው ነገር ላይ ለምንድን ነው ሰዎች ሁሉ መስማማት ያለባቸው? ይህ የምናየው ነገር ሁሉ ፍጡር እንደሆነና፣ ፍጡርም ያለ ፈጣሪ ሊገኝ እንደማይችል በዚህም የፈጣሪ መኖር እውነት መሆኑን የሰው ሁሉ ልቦና ያውቃል። <u>ሰዎች ሁሉ በዚህ ነገር ይስማማሉ</u> ።... "ሃይማኖት ሰዎች እርስ በእርሳቸው እንዲፋቀሩና የምሕረትን ሥራ እንዲሠሩ ታዛቸዋለች።

ስለዚህ በዘርዐ ያዕቆብ አስተሳሰብ አንድ አማኝ የሌላውንም ሃይማኖት አይነቅፍም ያከብራል እንጂ የሚል መልዕክት አለው። ምክንያቱም ራሱ ከደረሰበት ሃይማኖትን መሠረት ያደረገ በደል በመነሣት ሁሉም የኔ ብቻ ትክክል ነው በሚል በሚፈጠር ሙግት የሰው ልጆችን የሚጎዳ ተግባር እንደሚፈጸም ስለተረዳ ከርስ በርስ መፈቃቀር የተነሣ በሃይማኖት ውስጥ መከባበር እንደሚገባ ይገልጻል። በዘመናችንም በሃይማኖት ምክንያት የሚፈጠር ችግር ውጤቱ የከፋ መሆኑን መረዳት አስረጅ አያስፈልገውም።

## ስለቤተሰባዊነት እና ስለመተባበር

ዘርዐ ያዕቆብ እና ወልደ ሕይወት ለመተቸት የማይደፈሩ የሆኑ የሁሉንም ቤተ-እምነቶች ቅዱሳት መጻሕፍትን በመተቸት ከሚሞግቱበት አንደኛው ማኅበረሰባዊነት እና ቤተሰባዊ ጉዳዮች ላይ ነው። ለምሳሌ ዘርዐ ያዕቆብ እንዲህ ይላል፡-

> ወንጌል አባቱን እና እናቱን ሚስቱንና ልጆቹን ያልተወ ለእግዚአብሔር የተገባ አይደለም ይላል። ሆኖም ቤተሰብን መተው የሰውን ፍጥረት ሁሉ ያበላሻል፤ እግዚአብሔር ግን ፍጥረቱን በማበላሸት አይደሰትም። አባትና እናት ባረጁ ጊዜ ረዳት በማጣት እንዲሞቱ መተው ትልቅ ኀጢአት እንደሆነ ልቡናችን ይነግረናል። እግዚአብሔር እኮ ዐመፃን የሚወድ አምላክ አይደልም። (ክፍል 5)

ይህ አገላለጽ ቤተሰብን መተው እና አለመረዳዳት ምን ያህል ማኅበረሰባዊ ቀውስ እንደሚያስከትል ያስረዳል። ዘርዐ ያዕቆብ ከስደቱ መልስ ወደ እንፍራንዝ ገብቶ መኖር ከጀመረ በኋላም በሃይማኖት የእኔ ብቻ ትክክል ነው በሚል ተገቢ ያልሆነ ሙግት ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን ጉዳት የቀመሰ በመሆኑ፤ እንፍራንዝ ገብቶ መኖር ሲጀምር ስለ አኗኗሩ እንዲህ ይላል፡- "እኔም ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም እና በፍቅር እኖር ዘንድ ወደድኩ። የድካሜን ፍሬ እመገብ ዘንድ መረጥኩም" (ክፍል 11) በማለት ሲናገር፤ ተማሪው ወልደ ሕይወት ደግሞ ይህን ዕሳቤ ከፍ በማድረግ

“ሰው ብቻውን ካለሌላ ሰው ርዳታ ሊወለድ፣ ሊያድግ እና ሊኖር አይችልም” ከሚለው ዕሳቤ በመነሣት ማኅበረሰባዊ መተባበር ያለውን ወሳኝ ጠቀሜታ ይገልጻል። ከዚህም በላይ ስለመተባበር አስፈላጊነት ወልደ ሕይወት (በክፍል 13) ላይ እንዲህ ይላል፡-

> ሰው ወደ ፈጣሪው በቀረበ ጊዜ ወደ እሱም በጸሎትና በምስጋና ጸንቶ ከኖረ ከባልንጀራው ደግሞ ይርቅ ዘንድ አይገባውም። ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዲኖርና ከእነሱም ጋር ማኅበራዊ ሕይወት ተባባሪ ሆኖ እንዲኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እግዚአብሔር ሰውን በኑሮ በኩል ከሰው ጋር እንጂ ብቻውን በሕይወት ይኖር ዘንድ አልፈጠረውም። አንድ ሰው ለኑሮው የሌላ ሰው እርዳታ ያስፈልገዋል እንጂ ብቻውን በሕይወት ሊኖር አይችልም። ሁሉም ሰዎች እርስ በእርሳቸው እንዲረዳዱ ይገባቸዋል። ከሰው ማኅበርተኛነት የሚለዩ ግን የፈጣሪያቸውን ሥርዓት ያፈርሳሉ።

ይህ ሐሳብ የሰው ልጅ ከማኅበረሰባዊ ግንኙነት ውጭ መኖር እንደማይችል እና ይህም የአኗኗር ሁኔታ ፈጣሪ ለሰው ልጆች የሠራው የኑሮ ሥርዓት በመሆኑ ሠዎች እርስ በርስ እንዲተሳሰቡ የሚያስተምር ነው። ይሁን እንጂ በተለይም በአሁኑ ሰዓት በሰዎች መካከል እየተጠናወተ የመጣው ግለኝነት ተገቢ እንዳልሆነ ልንማርበት እንችላለን። ከዚህም በማከል ባልንጀራ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሲተረጉም እንዲህ ይላል፡-

> ባልንጀራ ማለት ዘመዶችንና ጎረቤቶችን ወይንም ወዳጆችን የሃይማኖት ወገኖችን ብቻ ካልሆነ በቀር ሌሎችን አያመለክትም የሚሉ የአዕምሮ ጎዶሎዎችን ትምህርታቸው መልካም አይምሰልህ። ሰዎች ሁሉ ባልንጀሮቻችን ናቸውና። ክርስቲያንም ሆኑ ሞስሊሞች፣ አይሁዶችም ሆኑ አረማውያን ሁላችንም አንድ ነን ሁላችንም ወንድማማቾች ነን ሁላችንም የአንድ አባት ሁላችንም የአንድ ፈጣሪ ፍጥረቶች ነን። ስለዚህ ሁላችንም እርስ በእርሳችን ልንፋቃቀር ይገባናል። በምንችለው ያህል ለሁሉም መልካም እናድረግላቸው እንጂ በማንም ላይ ክፉ አናድርግ (ክፍል 13) ።

ከዚህ በመነሣት የሁለቱም የዘርዐ ያዕቆብ እና የወልደ ሕይወት ዕሳቤዎች ሰዎች ለመረዳዳት ምንም ዓይነት መሥፈርትም ሆነ መለያ (ያ) ነገሮች ሊኖራቸው እንደማይገባ ያስተምራሉ።

## ስለትዳር እና ስለወሲብ

ስለትዳር አስፈላጊነት የዘርዐ ያዕቆብ ሓሳቡን የሚጀምረው የሰው ልጅ ካለው ተፈጥሯዊ ባሕርይ በመነሣት ነው። ይኸውም የሰው ልጅ በተሠራለት ተፈጥሯዊ ሥርዓት መሠረት ሩካቤ ሥጋ ከፈጣሪ ጥበብ ከተፈጥሮ ቀጣይነት፣ ሕግና ሥርዓት ጋር የተስማማ እና የተቆራኘ መሆኑን በመግለጽ ነው። ስለዚህም (በክፍል 5) እንዲህ ይላል፡-

> … ምክንያቱም በፈጣሪ ፈቃድና በተፈጥሮ ሥርዓት መሠረት የሰው ፍጥረት እንዳይጠፋ፣ ልጆችን ለመውለድ ወንድና ሴት በሩካቤ ሥጋ እንዲገናኙ ታዟል። ይህም ሩካቤ ሥጋ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በሕገ ተፈጥሮው የሠራለት ነው። እግዚአብሔር የእጁን ሥራ አያረክስምና ወሲብ ርኩስ ሊሆን አይችልም።

በዚህም ዘርዐ ያዕቆብ የትዳር አስፈላጊነትን የሚገልጸው በዋናነት ተገቢ በሆነ ሩካቤ (ግንኙነት) ትውልድ እንዲቀጥል በማለት ነው። በዚህም ሩካቤ ፈጣሪ የሠራው ተፈጥሯዊ ሕግ መሆኑን እንረዳለን። ከዚህም ባሻገር ዘርዐ ያዕቆብ አለማግባት እና ከአንድ በላይ ከብዙ ሴቶች/ወንዶች ጋር መጋባት እና መውለድን በጽኑ ይቃወማል። ለዚህም ምክንያት የሚያደርገው ደግሞ ሁለቱም ከተፈጥሮ ሕግ ጋር የሚጣረሱ ክዋኔዎች መሆናቸውን በማስረዳት ነው። ስለዚህም (በክፍል 5) ስለኣለማግባት፡-

> ሥርዓተ አውስቦ (ጋብቻ) የፈጣሪ ሥርዓት ሲሆን አለማግባት ግን ልጆች ከመውለድ ከልክሎና የሰውን ፍጥረት አጥፍቶ የፈጣሪን ጥበብ የሚያጠፋ እንደሆነ ልቦናችን ይነግረናል፤ ያስረዳናል። ካለ በኋላ፤

ከአንድ ወንድ እና ከአንዲት ሴት በላይ የሚደረግ ጋብቻንም ስሕተት መሆኑን በምክንያታዊነት ያስረዳል። ይህም እንደ ፈላስፋው ዕሳቤ በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለውን የቁጥር ምጣኔ በማሰብ አንድ ወንድ በርካታ ሴቶች ጋር ጋብቻ ቢፈጽም ባላገቡ ወንዶች ላይ ሚስት በማጣት ሊፈጠር የሚችለውን ማኅበረሰባዊ ችግር ያገናዘበ በመሆኑና ተፈጥሯዊውን ሕግ እንደሚያፈርስ በማሰብ ነው። ስለዚህም፡-

> … የሚወለደው ሰው ወንዱ እና ሴቱ በቁጥር እኩል ናቸው። በአንድ የተወሰነ አካባቢ ያሉትን ወንዶችና ሴቶችን ብንቆጥራቸው ለእያንዳንዱ ወንድ አንድ ሴት ትደርሳለች እንጂ ለእያንዳንዱ ወንድ ስምንት ወይም ዐሥር ሴት አይደርሰም። ተፈጥሮ ይህንን ያደረገችበት ምክንያት አንድ ለአንድ እንዲጋቡ ነው። አንድ ወንድ ዐሥር ሴት የሚያገባ ከሆነ ግን ሚስት የሌላቸው ዘጠኙ ወንዶች ይቀራሉ። ይህም የፈጣሪን ሥርዓትና የተፈጥሮን ሕግ ያፈርሳል። የጋብቻን ጥቅም ዋጋ ቢስ ያደርገዋል። ይላል

በዚህም መሠረት ዘርዐ ያዕቆብ ተፈጥሯዊ አይደለም ለሚለው ብቸኝነቱን ለመታደግ ትዳር ለመመሥረት ዐምስት መሥፈርቶችን ማሟላቱን እንረዳለን። የመጀመሪያው በጽሕፈት የሚያገኘውን የኢኮኖሚ ዐቅሙን ካረጋገጠ በኋላ በማስከተል ውበት፣ ሥነ ምግባር፣ ልባምነት (አስተዋይነት) እና ትዕግስት ሲሆኑ። ነገር ግን የውበትን ጉዳይ ቦታ አልሰጠውም። ያገባት ሒሩት ሁሉን ስታሟላ መልከ መልካም ግን አልነበረችምና ነው።

ከመምህሩ ዘርዐ ያዕቆብ ዕሳቤ ጋር በተመሳሳይ ወልደ ሕይወት ደግሞ ጋብቻ በፈጣሪ ለሰው ልጅ የተሠራ ትልቅ ጥበብ መሆኑን እንዲህ ይገልጸዋል (ክፍል 24)፡-

> ሴትና ወንድ ከአውስቦ ጋር የፈጠረ የፈጣሪ ትእዛዝ ነውና ሴት ከሌለችህ አግባ፤ ባል ከሌለሽ አግቢ። … አለማግባትን መውደድ የሰው ተፈጥሯዊ ባሕርይን የሚቃወም እና የፈጣሪን ሥርዓት የሚያፈርስ ነው። መጋባት ከፈጣሪ የእጅ ሥራዎች ሁሉ ይልቅ ትልቅና የተቀደሰ ጥበብ ነው።

በማከልም በመጋባት የሚገኘውን የሩካቤ ሥጋ ጣዕምና ጥቅም ትኩረት በመስጠት "መጋባት የተፈጥሮን ሕግ አጽንቶና አሳምሮ በዚህ ዓለም ላይ ካሉትም ጣዕሞች ሁሉ አስበልጦ በፈጣሪ ፈቃድ የተሠራ ስጦታ ነው። … ይህም የሰው ትውልድ እንዳይጠፋና የሰው ኑሮም እንዳይፈርስ ነው።" ይላል (ክፍል 24)።

የወልደ ሕይወት ዕሳቤ እንደ ዘርዐ ያዕቆብ ኣለማግባትን ከተፈጥሮ ሕግ ጋር አለመስማማት መሆኑን የመረመረ ሲሆን፤ ከአንድ በላይ መሔድንም (ማግባትንም) ደግሞ ዝሙት (ኃጢኣት) በመሆኑ ከፈጣሪ ጋር የሚያጣላ መሆኑን እንዲህ ይገልጻል፡-

> የአካልህ መጠን በደረሰ ጊዜ ሥጋህ የአውስቦን ፈቃድ ያሳይሃልና ፍጥረትህ ባልሆነው እንዳትበድልና ፈጣሪም በማግባት ያዘጋጀልህን ዋጋ እንዳታጠፋ፤ በረከቱንም ከአንተ እንዳታባርር በአስፈላጊው ጊዜ ሚስት አግባ። ቶሎ ብለህ አግባ እንጂ አትዘግይ። ከዝሙት ሽሽ። ዝሙት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሠራው ሥርዓት የወጣ ነውና ከአንዲትም ወደ ሁለተኛይቱ ሴት አትሒድ። ሴቷም ዝሙት አይጠቅማትምና ከወንድ ላይ ወንድ አትውደድ። (ክፍል 24)

ከላይ እንደተመለከትነው ዘርዐ ያዕቆብ ከተጠቀመባቸው የጋብቻ መሥፈርት ሐሳቦች ከፍ በማድረግ ወልደ ሕይወት ጋብቻን ለመፈፀም ወንዶች እና ሴቶች ያላቸውን ተፈጥሯዊ ሥነ አካላዊ ሁኔታን ግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚገባ እንዲህ ይላል፡-

> ትዕቢት እንዳይዛት መልከ መልካምና በጣም ሀብታም ሴት አታግባ። የአውስቦ ፍቅር ከትዕቢት ጋር አይስማማምና ሴትም እንዳይንቃትና ወደ ሌላ ሴት እንዳይሔድባት ትዕቢተኛና ጎይለኛ ወንድ አታግባ። መፋቀር ግን ከብዙ ሀብትና በዚህ ዓለም ካለው ክብረት ሁሉ ይበልጣል። ከወንድ ይልቅ ሴት አካል ቶሎ ይደርሳልና ፈጥኖም ስለሚያረጅ በሥምንት ወይም በዐስር ዓመት የምታንስህን ብታገባ ይሻልሃል። (ክፍል 24)

የወልደ ሕይወት ዕሳቤ ከዘርዐ ያዕቆብ ዕሳቤ ያደገ መሆኑን ከምንረዳበት እና በትዳር ውስጥ ስለሚፈጸም ሩካቤ ሥጋ ስላለው ጥቅም እና ፈጣሪ ለሰው ልጅ አስደሳች ከሆኑ ነገሮች ሁሉ በላይ አድርጎ በሥጋ ውስጥ የሠራው የፍትወት ስሜት መሆኑን ያስረዳል። ስለዚህም እንዲህ ይላል፡-

> … ጣዕም ባለው የአውስቦ ሥርዓታችሁም ተደሰቱበት። ይህም ጣዕም መጋባትና ሩካቤን ባዘዘ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕና የተወደደ ስለሆነ የምትሠለጥኑበት ነው። … ፈጣሪም በትልቅ ጥበብ የሩካቤን ጣዕም የሚያወጣ ምሥጢርን በሥጋችን ውስጥ አደረገልን። … የሕይወት ጎይልና የምግብ ጣዕም ከምድር እንደወጣ ሁሉ፤ የመብልን ጣዕምም ስንሻ ሕይወታችን እንደሚጠነክር ሁሉ እንዲሁም የሰው ልጆችን ዘር ለማብዛት ከፍጥረታት ሁሉ ከፍ ያለ፤ ከጣዕምም ሁሉ የበለጠ ጣዕም የሚወጣ ድንቅ የሆነ የፍትወት ስሜትን በመሬታዊ ሥጋችን ውስጥ አደረገልን። እኛም ይህን ጣዕም ፈጣሪያችን በሠራልን መንገድ ስንፈልገው ዘራችንን በአምሳያችን እናበዘዋለን። (ክፍል 24)

ከዚህም በላይ ወልደ ሕይወት በሩካቤ ጊዜም ሊኖር ስለሚገባው የእርካታ መናበብ እንዲኖርም በግልጽ እንዲህ ያስተምራል፡-

> . . . ፈጣሪህን በማመስገንና በማድነቅ ወደ ሚስትህ ቅረብ። ወደ እሷ በገባህ ጊዜም የሩካቤን ጣዕም ከሚስትህ ጋር ተካፈለው እንጂ ለብቻህ አትሻው። ከአንተ እርካታ ኋላ ቀርታ ጣዕሙ እንዳይጎድልባት፤ እርሷም በአንተ እስከትደሰት ቆያት እንጂ እግዚአብሔር የሰጣትን ፈንታዋን ከልክለህ በችኮላ አታድርገው (ዘርህን አታፍስሰው)። ይህንንም ፍቅር ካላደረክላት ታዝንብሃለች፣ ትንቅሃለች። ጋብቻህም ለእግዚአብሔር በረከት የተዘጋጀ አይሆንም።

በማለት ወልደ ሕይወት በትዳር ውስጥ ሆነው በሚፈጽሙት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ጊዜ ሊኖር ስለሚገባው የእርካታ መናበብ ወንድ ሊያደርግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ይገልጻል። ይህም በትዳር ውስጥ የሚደርግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሁለቱ ጾታዎች መካከል ያለው መናበብ ለትዳር መጽናትም ሆነ መፍረስ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ጥናቶች ያመለክታሉ (Khan and London, 1991; Whyte, 1990)። ከዚህ አንጻር በዘመኑ (በ17ኛው መቶ ክፍል ዘመን) ኢትዮጵያውያን የደረሱበትን የሰብኣዊ/ የተፈጥሯዊ ሕግ ምርምር ደረጃው ከፍ ያለ መሆኑን እንገነዘባለን።

## ስለትዳር ተግዳሮት እና ፍች

በጋብቻ ላይ ስለሚፈጸም ፍች በዘርዐ ያዕቆብና በወልደ ሕይወት መካከል ያለው ተመሳሳይነት ሁለቱም ፍችን አለመቀበላቸው ነው። ዘርዐ ያዕቆብ ለትዳር መደናቅፍ የሚሆኑትን በመጀመሪያ የዘጋቸው ስለሆነ ስለፍች የተነተነው ነገር የለም። ተማሪው ወልደ ሕይወት ደግሞ ፍልስፍናው ዘርዐ ያዕቆብን መሠረት ያደረገ እና በአንዳንድ ሐተታውም መምህሩ በደንብ ያልመረመረውን በጥልቅ ለመተንተን የተጠመደ ይመስላል። ለምሳሌ ዘርዐ ያዕቆብ ያልተነተነውን የፍች ሁኔታ በወልደ ሕይወት ሐተታ ተገልጾ ይገኛል።

ይህንም ትዳር ለጊዜያዊ ሕይወት የሚመሠረት ተቋም ሳይሆን ዘላለማዊ የሆነ ሰብኣዊ መስተጋብር ስለሆነ ለፍች ምንም ዓይነት ምክንያት አለ አይልም። ከላይ እንደተመለከትነው ባልና ሚስት የሚፈጽሙት የሩካቤ ሥጋ መናበብ ፍቅርና መከባበርን የሚፈጥር መሆኑን በማስረዳት ይህ በጥንቃቄ መደረግ እንዳለበትና ለትዳርም መጽናት ቁልፍ ነገር መሆኑን ገልጿል። ከዚህ ባሻገር ለትዳር ውበቱ የሆነው ፍቅር ላለመፋታት አዎንታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር መሆኑን እንዲህ ይገልጻል፡-

> ሁሉን የሚያሳምረው ፍቅር ነውና በእርሱ ጽና። ብዙ ወንዶች ሚስቶቻቸውን፤ ብዙ ሴቶችም ባሎቻቸውን ለጥቂት ዘመን እንደሚወዱ አትሁን። ከዚህ በኋላ ጋብቻቸውን ይጠሉና አንዱ ለሌላኛው ከባድ ይሆናሉ።... አንተ ግን ልብህን አጽናው። እግዚአብሔር መጀመሪያ ላይ ያደረገልህም ከሁለተኛው ይሻልሃልና በመጀመሪያ ጋብቻህ ጽና። የጠባያችን ተለዋወጭነት ግን ለወንድ ሌላ የተሻለች ሴት ያሳየዋል፤ ለሴትም ሌላ የበለጠ ወንድ ያሳያታል። ይህ ስህተት ነው። (ዘርዐ ያዕቆብ፣ ክፍል 25)

ከዚህም በላይ ወልደ ሕይወት ፍቺ ጉዳት እንጂ ምንም ጥቅም እንደሌለው በምሳሌ ያስቀምጣል (ክፍል 25 ይመልከቱ) ።

## ስለልጆች አስተዳደግ

ዘርዐ ያዕቆብና ወልደ ሕይወት ከሚስማሙበት አንደኛው ዕሳቤ መጋባት ትውልድ እንዲቀጥል የሚደረግበት የተፈጥሮ ሕግ መሆኑን ነው። ልጆችም ከተወለዱ በኋላ ወላጆቻቸው እነሱን በመወደድ ማሳደግ የሚገባቸው እና በምንም ምክንያት ልጆች መተው እንደሌለባቸው ያስረዳሉ። ስለዚህም ዘርዐ ያዕቆብ "ልጅን መተው ልጆቻቸውን ከማይተው ከዱር አራዊት የከፋ ነው" (ክፍል 5) በማለት ሲናገር፤ ወልደ ሕይወት ደግሞ "ልጆች የእናንተ ምትክ ናቸውና በእነሱ ተደስታችሁ ውደዷቸው። በጥበብና በጥንቃቄም አሳድጓቸው" (ክፍል 28) በማለት ለልጆች ማደግ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው፣ መውደድ እንደሚገባና እነሱንም መተው ከእንስሳት ማነስ መሆኑን ያስረዳሉ። ከዚህም በማስከተል ልጆች ግብረ ገብ እንዲሆኑ የወላጆች መልካም አርዓያነት ወሳኝ ስለመሆኑ "...የመልካም ምግባርና ጥበብ አርዓያ ሁኗቸው እንጂ በአርዓያችሁ ክፉ ምግባርን እንዳይማሩ የክፉ ምግባር አርዓያ አትሁኗቸው።" በማለት ኀላፊነትን ለወላጆች ይሰጣል።

ከዚህም ባሻገር ልጆች ባጠፉ ጊዜ መገሠፅ እንዳለባቸው - "በልጅነታቸው ካልተገሠፁ ክፋታቸው ያድግባቸውና በኋላ ለመመለስ አስቸጋሪ ይሆናሉ" በማለት ልጆችን በተገቢው መንገድ መገሠፅ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻል። በማከልም የሌሎችን መልካም ሰዎች አርዓያነት በመወሰድ፣ በታሪክና በምሳሌ እያደረጉ ልጆችን ማስተማር በተሻለ የልጆችን ስብእና የሚያንጽ መሆኑንና በዚህም ስለሚገኘው ግብረ ገብ የሆነ የትወልድ ቀረጻና ሰብኣዊ ትርፍ እንዲህ ያስተምራል (ክፍል 28) ፡-

> ... ከክፉ ምግባር እንዲርቁና ሥነ - ሥርዓትንም እንዲማሩ የሌሎችን ሰዎች አርዓያ፣ ታሪክና ምሳሌ እያነሣህ ዘወትር አስተምራቸው። ... የእጅ ሥራን አስተምራቸው። ይህንን በማድረግህ ልብህ አይድከም። ልጆችህን ለማሳዳግ ይህን ሁሉ ችግር የተቸገርከውን፤ የደከምከውን ድካም፣ የታገስከውንም ትዕግሥት ሁሉ እግዚአብሔር ይቆጥረልሃል፤ ታላቅ ዋጋም ይከፍልሃል። ልጆችህም ሽምግልናህን ያስደስቷታል። ሽበትህንም በሰላምና በማይጠፋ ተስፋ ወደ መቃብር ያወርዱታል።

በዚህ ዕሳቤ ውስጥ ወልደ ሕይወት ስለልጆች የስብእናን መቀረጽ ሙሉ ኃላፊነትን ለወላጆች ሰጥቷል። ልጆች ከልጅነታቸው ጀምሮ የቤተሰብ አርዓያነት የሚያስፈልጋቸው፤ ትምህርት እና የእጅ ሥራ መማር እንደሚገባቸው፤ በተለይ ደግሞ በዘመናዊው ዓለም ቅቡል የሆነው ልጆችን በታሪክና ምሳሌ ማስተማር ውጤታማ እንዲሚያደርግ እንረዳለን።

## ስለትምህርት እና እጅ ሥራ (ጥበብ) ጥቅም

ዘርዐ ያዕቆብና ወልደ ሕይወት ትምህርትን እና የእጅ ሥራን መማር ለሰው ልጅ አስፈላጊ መሆናቸውን ይገልጻሉ። የእነሱም ሕይወት ከመማር፣ ከመመራመር እና ከእጅ ሥራ ጋር ፍጹም የተቆራኘ ነበር። በተለይም ዘርዐ ያዕቆብ መማሩ እና የእጅ ሥራ (ጽሕፈትን ማወቁ) ለኑሮው የጠቀመው መሆኑን እንረዳለን።[8] ከዚህም ባሻገር ትምህርት እና እጅ ሥራ የሰውን ልጅ ሕይወት የሚሳምሩ (የሚያበለጽጉ) መሆናቸውን ሲገልጽ፡-

---

8 **በመካከለኛው ዘመን ጽሕፈትን ማወቅ ደኅስ ያለ ጥቅም ያስገኝ ነበር። የቤተክህነት አባቶች ምሁራኑን እንዲጽፉ ከማያደርጉት ልማድ ባሻገር ነገሥታቱ ለስማቸው ማስጠሪያ በሚል ለሚጽፉ ሰዎች ልዩ ማበረታቻ ይሰጡ ስለነበር በርካታ የጽሑፍ ሀብቶች እንዲጻፉ አድርገዋል።** (**አንደርዜይ እና ዮዓና**፣ 2006 **እና ሰሎሞን ዮሐንስ** (**ዲያቆን**)፣ 2001)።

> ፈጣሪያችን ንብረታችንን በዕውቀታችንና በሥራ እንድናሳምረው ይፈልጋል። ምክንያቱም ለዚህ የሚሆን ልቦናና ችሎታ ሰጥቶናል። ስለዚህ የእጅ ሥራን መሥራት የፈጣሪ ፈቃድ ነው፤ ምክንያቱም ያለ ተግባረ እድ ለሕይወት የሚያስፈልገንን ማግኘት አንችልም (ክፍል 9) ።

በማለት እጅ ሥራ ጥቅሙ ከፍ ያለ መሆኑን ያትታል። ከዚህ አንጻር ይህ ጠቃሚ ተግባር በጥንታዊ ኢትጵያውያንም ዘንድ የነበረ ዕሳቤ እና ክዋኔ መሆኑን እንገነዘባለን። በዘመናችንም ያለ እጅ ሥራ ትምህርት (Vocational education) እድገት እንደማይገኝ ሲነገር እንሰማለን። ዘርዐ ያዕቆብ ይህንን ሲል የእሱ ተማሪ የነበረው ወልደ ሕይወት አስፋፍቶ ተንትኖታል። ስለዚህም "ትምህርትን ለመማር አትድከም…።" ይህን ካለ በኋላ ትምህርት ማብቂያ እንደሌለው ሲናገር፡-

> በአንድ ትምህርት ብቻ አትኑር እሷ ክፉ ናትና። ብዙ ሥራዎች እንድታገኝ ትምህርት የተባለውን ሁሉ ተማር። እስቲ ንቦች የበርሃ አበቦችን እንዴት አድርገው እንደሚቀስሙ ተመልከት። ንቦች ከሁሉም አበባዎች እየዞሩ ምግባቸውን ይሰበስባሉ እንጂ በአንድ እርሻና በአንድ አበባ ብቻ አይኖሩም። በዚህ ትጋታቸው ማርና ሰምን ያስገኛሉ። ማርም መጠጥነቱ የቀን ደስታን ሲያስገኝ፤ ሰሙ ደግሞ በጧፍነቱ የሌሊት ብርሃን ይሆናል። እነዚህ ጥቅሞች በመትጋት ይገኛሉ። ይላል (ክፍል 17)

ይህ የወልደ ሕይወት ዕሳቤ በአንድ የትምህርት ዘርፍ ወይም ሞያ ብቻ ሠልጥነው ነገር ግን የሌላውን ሞያ ወይም ትምህርት ለሚንቁ ምሁራን ትልቅ እርምት የሚሰጥ ዕሳቤ ነው። በተጨማሪም ስለ እደ ጥበብ (እጅ ሥራ) ጥቅም እና አስፈላጊነት ሲናገር፡-

> ለኑሮህ ተስማሚ የሆነውን የእጅ ሥራ ውደድ። እንድትጠቀምበትም በእርሱ ዕውቀትን አግኝና እርሱ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነውና የእጅን ሥራ በመሥራት አትፈርበት። ያለ እጅ ሥራ ግን የሰው ፍጥረት ሁሉ ይጠፋና ኑሮውም ሁሉ ይፈርሳል። አንተ ግን እጅ ሥራ ለድሆች፣ ለሠራተኞች፣ ለአንጥረኞችና ለአናጺዎች እንዲሁም ለገባር ልጆች እንጅ ለታላላቆች እና ለባለፀጋዎች አይገባም አትበል።… ሁሉም በመሠረታዊ ፍላጎቱ እኩል አይደለምን? በማለት ይጠይቃል ። (ክፍል 18)

በዚህ ጥያቄ ውስጥ የእጅ ሥራ ለሰው ልጅ ሕልውና ወሳኝ መሆኑን ያስረዳል። ባለፉት ዘመናት በማኅበረሰቡ ዘንድ እጅ ሥራ ባለእጅ፣ ቀጥቃጭ፣ ወዘተ. የሚል ስያሜ የሚሰጣቸው የተወሰኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሥራ መሆኑ ይታሰብ ነበር። ነገር ግን ዘርዐ ያዕቆብ የእጅ ሥራ የሚሰጠውም ዋጋ ዝቅ ያለ መሆኑ ተገቢ ኣለመሆኑን በማስረዳት እጅ ሥራ ለሰው ልጆች የሕልውና መሠረት መሆኑን ይሞግታል። ወልደ ሕይወትም ይህንን የማኅበረሰብ አስተሳሰብ ትክክል ኣለመሆኑን በመሞገት ሰው ኑሮውን እና ሕይወቱን ለማስቀጠል የሚስማማውን እጅ ሥራ መሥራት ግድ እንደሆነ ይገልጻል።

## ግብረ ገብ ስለመሆን

በዘመናችን እያጣነው ያለው ኢትዮጵያዊ ማንነት አንደኛው ግብረ ገብነት ነው። ግብረ ገብ ስለመሆን ዘርዐ ያዕቆብ የሚጀምረው ፈጣሪ የሰው ልጅን ክፉና ደጉን መለየት ከሚያስችለው ዕውቀት ጋር መፈጠሩን በመግለጽ ነው። ወልደ ሕይወት ደግሞ የሰው ልጅ የተሰጠው ዕውቀት፤ ፈጣሪ የሰጠውን ነገሮች በመመርመር እውነተኛውን ጥበብ የሚከፍትበት ቁልፍ ነው በማለት ነው። በዚህም መልካም እና ክፉ የሆነውን ነገር መለየት የሰው ልጅ ግብረ ገብ ለመሆንና ላለመሆን ያደርሰዋል። ስለዚህም እንዲህ ይላል፡-

> ፈጣሪ ሰውን የምግባሩ ጌታ እንደፈለገ ክፉ ወይም መልካም እንዲሆን የሥራው ባለቤት አድርጎ ፈጠረው። ሰውም ክፉና ሐሰተኛ መሆንን ቢመርጥ ለክፋቱ የሚገባውን ቅጣት እስኪያገኝ ድረስ (የፈለገውን ለመሆን) ያስችለዋል። ነገር ግን ሰው ሥጋዊ ነውና ለሥጋው የሚሻለውን ይወዳል። ለሥጋው የሚያስፈልገውን በመልካምም ሆነ በክፉ ባገኘው መንገድ ሁሉ ይፈልጋል። እግዚአብሔር ግን ሰውን የፈለገውን እንዲሆን ምርጫን ሰጠው እንጂ ክፉ አድርጎ አልፈጠረውም። በዚህም ምርጫው ክፉ ቢሆን ለቅጣት፤ ምርጫው መልካም ከሆነ ደግሞ መልካም ዋጋ ለመቀበል የተዘጋጀ እንዲሆን አድርጎ ፈጠረው። (ክፍል 4)

ከዚህ ዕሳቤ አንጻር በዘርዐ ያዕቆብ ዘንድ የሰው ልጅ ክፉ ወይም ደግ ለመሆን ቀድሞ የተወሰነበት ውሳኔ ሳይሆን ክፉ ወይም ደግ የመሆን የግል ምርጫ መሆኑን እንረዳለን። በዚህም የሰው ልጅ ሊሆን የፈለገውን እንጂ ቀድሞ የተወሰነለት (የተወሰነበት) ነገር (Predestination) አለመኖሩን እንረዳለን። ስለዚህ ሰው የራሱን ዐዋቂነት በመጠቀም ክፉ ወይም መልካም፤ እውነተኛ ወይም ሐሰተኛ፤ ሙሰኛ (ሌባ) ወይም ቁጥብ መሆን እንደሚችል ያስገነዝበናል። ወልደ ሕይወትም የሰው ልጅ መልካሙንና ክፋውን፤ እውነቱን እና ሐሰቱን የሚለይበት ብርሃን ልቦና እንደተሰጠውና እውነት ያልመሰለውን መተው እንደሚችል (ክፍል 5 ላይ) ይነግረናል። በዚህም የሰው ልጅ በራሱ መልካምን እና ክፉን መከተል እና መሆን እንደሚችል ተፈጥሮው የሚፈቅድለት መሆኑን እንረዳለን። ከዚህም በማከል (ክፍል 9 ላይ) የሰው ልጅ ለምን የፈጣሪ ቅጣት እንደሚጠበቀው በመጠየቅ "ፈጣሪ ለምን ይቀጣናል?" ብሎ አመራማሪ ጥያቄ ካነሣ በኋላ እንዲህ ብሎ ይመልሳል፡-

> እግዚአብሔር ሕላዌው ፍጹም ነው። ደስታውም ለዘላለም አይጎድልም ሊያስቆጣውም የሚችል የለምና ከቶም አይቆጣም፤ በመዓቱም የሚመታን አይደለም። ነገር ግን ፈጣሪ ለእኛና ለፍጥረት ሁሉ በአንድነት የሠራልንን ሕግጋት ባፈረስን ጊዜ ቅጣትን እኛው በራሳችን ላይ እናመጣዋለን።

በማለት የሰው ልጅ ቅጣት የሚያገኘው ራሱ ወዶ ፈቅዶ በሠራው ክፉ ሥራ ብቻ እንጂ ፈጣሪ ክፉ እንዲሠራ እያሳየው፣ እያለማመደው በሚያደርገው ድርጊት አይደለም። ክፉ እንዲሠራ የሚያስገድደውም አይደለም። ምክንያቱም የሰው ልጅ ክፉ እና ደጉን የሚያስለየው አዕምሮ ስለተሰጠው ነው። ስለዚህ የሰውን ልጅ ለቅጣት ወይም ለሽልማት የሚዳርገው ከተሰጠው የተፈጥሯዊው ዕውቀቱ በመነሣት ክፉ ወይም ደግ የሆነውን ለይቶ በሚያደርገው የድርጊት ውጤት ነው። በአጠቃላይ የሰው ልጅ ግብረ ገብ ለመሆን ከፈጣሪ የሚታደለው ሽልማት ሳይሆን የራሱ ወይም የግሉ መሻት ግብረ ገብ የመሆን ውጤት ነው የሚል አስተምህሮ አለው። ምክንያቱም የሰው ልጅ በተፈጥሮው ዐዋቂ ሆኖ ስለተፈጠረ።

በአጠቃላይ በዘርዐ ያዕቆብም ሆነ በወልደ ሕይወት ዕሳቤ የሰው ልጅ ክፉ ወይም ደግ ለመሆን የተፈጠረ፤ ክፉ ወይም ደግ ብቻ ሆኖ እንዲቀር የተወሰነለት/ የተወሰነበት፤ ወይም ከእናቱ ማኅጸን ክፉ ወይም ደግ ሆኖ የተወለደ ፍጡር ሳይሆን የራሱ የሆነ ባለ አዕምሮ፤ ከዐዋቂነቱ የተነሣ የራሱን ክፋትና ደግነት የሚወስን ፍጡር መሆኑን እንገነዘባለን። ስለዚህ ግብረ ገብ መሆን የሰው ልጅ የራሱ ውሳኔ ስለሆነ ደግ እንሁን የሚል አስተምህሮ አላቸው።

# ማጠቃለያ እና አስተያየት

## ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ዘርዐ ያዕቆብ እና ወልደ ሕይወት በተባሉ ኢትዮጵያውያን ፈላስፎች የተደረሱ የፍልስፍና ድርሳናት ላይ ማኅበረሰባዊ ፍልስፍናዎች ላይ የሚያጠነጥኑትን ሐሳቦች ለይቶ በማውጣት ለማኅበረሰብ ሊያበረክቱ በሚችሉ አስተምህሮቻቸው ላይ ትንተና መስጠት ነው። ጥናቱ መሠረት ያደረገው በጽሑፍ ሥራዎች ላይ በመሆኑ ዓይነታዊ (qualitative) የጥናት ዘዴን ጥቅም ላይ አውሏል። የዘርዐ ያዕቆብ እና የወልደ ሕይወት የፍልስፍና መጻሕፍት እንደ መጀመሪያ ደረጃ የጥናቱ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል። እንደ ሁለተኛ ደረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ የዋሉት የተለያዩ መጻሕፍት እና የምርምር ሥራዎች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ቃለ መጠይቅ ሌላው የመረጃ ምንጭ ነበር። በመሆኑም ጥናቱ ማኅበረሰባዊ ፍልስፍናን ማዕከል በማድረግ የማኅበረሰባዊ ፍልስፍና ንድፈ ሐሳባዊ ዕይታዎችን ከገላጭ የትንተና ዘዴ (discriptive analysis) ጋር በማቀናጀት ለማኅበረሰብ ሊበጁ የሚችሉ ሰባት የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችን ለይቶ በማውጣት ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል።

ጥናቱ ሀገር በቀል ፍልስፍና ላይ ያተኮረ በመሆኑ ፍልስፍና ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያ የነበረ አንድ የዕውቀት ዘርፍ መሆኑን መገንዘብ ያስችላል። ምክንያቱም ፍልስፍና ነገሮችን በጥልቀት፣ በምክንያታዊነት እና በተጠየቃዊነት በመመርመር፣ በመጠየቅ፣ በመተቸት እና በመሞገት ወደ ድምዳሜ የሚደርሱበት የዕውቀት ዘርፍ ነው። ከዚህ አንጻር የዘርዐ ያዕቆብ እና የወልደ ሕይወት ሐተታዎች የላቁ የፍልስፍና ዕሳቤዎች የተንጸባረቁባቸው በመሆኑ እና በርካታ ሀገር በቀል ማኅበረሰባዊ ጉዳዮችን እያነሡ የሚሞግቱ እና ድምዳሜ ላይ የሚደርሱ በመሆናቸው ዘመን ተሻጋሪ ኢትዮጵያዊ ፍልስፍና የሚባል መኖሩን ማሳያ ናቸው። በሁለቱም ፍልስፍናዎች በዋናነት ተተኳሪ የተደረገው ማኅበረሰባዊ ጉዳይ በመሆኑ ማኅበረሰባዊ ፍልስፍናቸው የጎላ ነው ማለት ይቻላል። በዚህም ሁለቱም ፍልስፍናዎች ለማኅበረሰብ ችግር መፍትሔ መሆን የሚችሉ ምክረ ሐሳቦች ማግኘት የሚቻልባቸው ዕሳቤዎች ናቸው።

በአጠቃላይ በዘርዐ ያዕቆብ እና በወልደ ሕይወት የተደረሱት የፍልስፍና ድርሳናት ከዘመናቸው (ከ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን) ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለውን ማኅበረሰብ ለያንጹ እና ሊያበጁ የሚችሉ ዘመን ተሻጋሪ ሐሳቦችን ያዘሉ ሥራዎች ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል።

# አስተያየት

በዘርዐ ያዕቆብ እና በወልደ ሕይወት የተደረሱት የፍልስፍና መጽሐፎች ነገሮችን በጥልቀት በመርመር ለማወቅ የሚደረግ የአስተሳሰብ ልሕቀት (ፍልስፍና) በኢትዮጵያ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ የነበረ የዕውቀት ዘርፍ መሆኑን ማስረጃ ስለሚሆኑ እነዚህን ሁለት መጽሐፎች ዋቢ በማድረግ የቀደሙ በተለይ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍትን በትኩረት ማጥናት ይገባል። ለዚህም የግዕዝ ቋንቋን ማጥናት ግድ ስለሚል፤ አሁን እየተሰጠው ያለው ትኩረት አበረታች ቢሆንም ቋንቋውን ከማበልጸግ እና ከማሳደግ አንጻር ክፍተት ስለሚታይ የበለጠ በትጋት መሥራት ይገባል።

ጥናቱ መሠረት ያደረገው ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና ላይ ነው። ይህ የፍልስፍና ዓይነት አንድ ማኅበረሰብ በመልካም ሥነ ምግባር የሚታነጽበትን ሐሳብ የሚያመላክት ዘርፍ ነው። በተለይ በአሁን ሰዓት በሀገራችን ግብረ ገብነት እየቀጨጨ መምጣቱን እንረዳለን። ቢሆንም ግብረ ገባዊ ማንነታችን መገኛ ከእኛነታችን ከተቀዳው የዕውቀት ምንጭ ስለሚሆን የጥንታዊ ጽሑፎቻችንን በጥናት በመለየት፣ በማስተዋወቅ እና ጥቅም ላይ በማዋል እየተጠናወተን የመጣውን ኢ-ግብረ ገባዊነት በማስወገድ፤ ግብረ ገባዊ ማንነታችንንም ከጠፋበት ፈልገን ልናገኝ እንችላለን። ለዚህም የዘርዐ ያዕቆብ እና የወልደ ሕይወት የፍልስፍና አስተምህሮዎች ካላቸው አካታችነት አንጻር ከግብረ ገብ ማስተማሪያ መጻሕፍት ጋር አቀናጅቶ በማቅረብ በትምህርት ቢሰጡ ትውልዱን በሥነ ምግባር ለመቅረጽ አበርክቷቸው የጎላ ሊሆን ይችላል።

በዘርዐ ያዕቆብ እና በወልደ ሕይወት የተደረሱት የፍልስፍና ድርሳናት ለፊርጀ ብዙ ችግሮች መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ሐሣቦች ሊገኙባቸው የሚችሉ የጽሑፍ ሀብቶች ናቸው። ስለሆነም የማኅበረሰብ ሳይንስ አጥኚዎች፣ የሃይማኖት፣ የሥነ ማኅበረሰብ (Sociology) ፣ የሥነ ሰብእ (An-

tropology)፣ የቤተሰብ እና የማኅበረሰብ አማካሪዎች፣ የታሪክ፣ የሥነ ልቦና፣ የሕፃናት አስተዳደግ እና የመሳሰሉ ባለሞያዎች ትኩረት ሰጥተው ቢመረምሯቸው ለሞያቸው ችግር ፈቺ የሚሆኑ ሐሳቦችን ሊያገኙባቸው ይችላሉ።

## ዋቢዎች


ብሩሕ ዓለምነህ። (2010) ። የኢትዮጵያ ፍልስፍና። አዲስ አበባ። አሳታሚ አልተገለጸም።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ። (1951) ። የኢትዮጵያ ታሪክ፡ ኑብያ አክሱም ዛጉዬ እስከ አጼ ይኩኖ አምላክ ዘመን መንግሥት 1ኛ መጽሐፍ። አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት።

አምሳሉ ተፈራ። (2011) ። ነቅዐ መጻሕፍት። አዲስ አበባ፤ ጃጃው አሳታሚዎች።

አስረስ የኔሰው። (1951) ። ትቤ አኩስም መኑ አንተ። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ኢያሱ በሬንቶ። (2010) ። "ተግባራዊ ፍልስፍና (Practical Philosophy) በ17ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ፡ ሐተታ ወልደ ሕይወት እንፍራንዛዊ"፤ በዐባይ የባህል ማዕከል 3ኛው ሀገር አቀፍ ኮንፈረንስ 2009 ዓ.ም የቀረበ ዐውደ ጥናት መድብል ላይ የታተመ፤ 93 - 136።

ዓለማየሁ ሞገሥ። (1961) ። ሐተታ ዘርዐ ያዕቆብ ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ። አዲስ አበባ፤ በኀይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ለመመረቂያ ጽሑፍ የተዘጋጀ።

ጌታቸው ኀይሌ። (2006) ። ሐተታ ዘርዐ ያዕቆብ በመባል የሚታወቀው የወርቄ የሕይወት ታሪክ ። ሚኖሶታ ኮሌጅቪል።

ፈቃደ ሥላሴ ተፈራ (ሊቀ ጉባኤ) ። (2010)። ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት አዘጋጃጀት። አዲስ አበባ፤ አአዩ ማተሚያ ።

Audi, R. (2005). "Philosophy" in Borchert D.M. (Ed.) *Encyclopedia of Philosophy* (2nd Ed.),. Thomson Gale, a part of the Thomson Corporation., 2006, 7, 325 – 337.

Bekele Gutema and Charles C. Verharen. (2013). *"Introduction", African Philosophy in Ethiopia, Ethiopian Philosophical Studies II with A Memorial of Claude Sumner*, USA: Library of Congress Cataloging-in-Publication.

Getatchew Haile. (2005). '*Ge'ez Literature' in EAE*, vol.2, 736 – 741

Harden, J. M. (1926). *An Introduction to Ethiopic Christian Literature.* London: The Macmillan Co.

Khan, J., and K. London. (1991). Premarital Sex and the Risk of Divorce, Journal of Marriage and the Family, 53, 545-555.

Levin, D.N. (1974). *Greater Ethiopia: The Evolution of a Multiethnic Society.* Chicago & London: The University of Chicago Press.

Merriam-Webster. (2021). "*Social Philosophy".* Retrieved on 24 Sep. 2021, from https://www.merriam-webster.com/dictionary/social%20philosophy. Accessed

Messay Kebede (2004). *Africa's Quest for a Philosophy of Decolonization.* Editions Rodopi B.V., Amsterdam - New York, NY 2004 Printed in the Netherlands

Pedersen, Jorgen. (2012). *Social philosophy: A Reconstructive or Deconstructive Discipline? Philosophy and Social Criticism*, psc.sagepub.com, 38(6) 619–643.

Presbey, Gail M. And George F. McLean. (2013). *The Significance of Claude Sumner Sj's Contribution to African Philosophy. In African Philosophy in Ethiopia,* Ethiopian Philosophical Studies II. Series

II. Africa, Volume 15.

Saar, Martin. (2018). *X—What Is Social Philosophy? Or: Order, Practice, Subject. Meeting of the Aristotelian Society held at Senate House, University of London,* The Aristotelian Society Proceedings of the Aristotelian Society Vol. cxviii, Part 2, 208-223.

Sergew Hable Selassie. (1972). *Ancient Medieval History to 1270.* Addis Ababa: United Printers

Sumner, C. (1981). *Ethiopian Philosophy, The Life and Maxims of Skendes.* Addis Ababa University, Addis Ababa. Vol. IV.

------------- . (1985). *Classical Ethiopian Philosophy*. Addis Ababa: Commercial Printing Press.

-------------. (1994). *Classical Ethiopian Philosophy*. Los Angeles: Adey Publishing Co.

Tadesse Tamrat. (1972). *Church and State in Ethiopia.* Addis Ababa: AAU Press.

Verharen, Charles. (1996). *A Cultural Introduction to Philosophy. Teaching Philosophy,* 19:1 March, 1996, 65-80.

Whyte, M. (1990). *Dating, Mating and Marriage:* New York: Random House.